**International Ethiopian Woman Organization IEWO**

**ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት (ዓኢሴድ)**

IEWO, 1515 South 4th street #1801, Minneapolis, MN 55454, USA

# ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ሰብአዊ መብት ረገጣን ይቃወማል

የሴቶች ጥያቄ የሰብአዊ መብት ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም የመብት መስተጓጎል ሆነ መረገጥ ድርጅታችን አጥብቆ ይቃወማል። በሃገራችን ኢትዮጵያ ዜጎች ይታሰራሉ፣ ደብዛቸው ይጠፋል፣ ጭራሹን በሰላማዊ ሰልፍ ላይ ወጣቶችን ይገደላሉ፣ በሃሳብ ልዩነት ተቃዋሚ ተብለው በጠራራ ፀሐይ ታድነው ይገደላሉ ወዘተ...። እነዚህ ሰማእታት የህዝቡን መብት ማስከበርና አገራቸው የተሻሻለች ለሁሉም ወገን የምትመች አገር እንድትሆን የተዋደቁ በመሆናቸው መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሊያከብራቸው ይገባል።

ተዲ አፍሮ «አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቸ መጣ » ብሎ በመዝፈኑና ለሚወደው ህዝቡ ያለው ፍቅር ላቅ ያለ በመሆኑ « አይነጋም ወይ ሌቱ ለኢትዮጵያ » ብሎ በማስተጋባት ዜጎቹን በወገንተኛ ዘፈኖቹ ሰላነቃቃ እንጂ ሰው ድጦ በመጥፋቱ መቼ ሆነ የታሰረው።

ወ/ሮ መሶብወርቅም ቢሆኑ የድርጅታቸውን ጋዜጣ የሚያዘጋጁ አኩሪ ኢትዮጵያዊት ሴት በመሆናቸው የሳቸውን አርአያ በመከተል ሌሎችም እንዳይከተሉ ለማስፈራራትና መቀጣጫ ለማድረግ ነው በእስር ሲንገላቱ የከረሙት ።

ወ/ት ብርቱኳን ሚደቅሳም በዘረኛና አምባገነን ስርዓት እንደገና መታሰራቸው ማናቸውም ዜጋ መቃወም አለበት። ማንኛውም ሰው በፖለቲካ እምነቱ ሆነ ውገናው ምክንያት መታሰር የለበትም ብለን እናምናለን። በዚህ ምክንያት መታሰርና መንገላታት የሰብ አዊ መብት መርገጥ ስለሆነ ሁላችንም ዜጎች ባንድነት እንድንቃወመው ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የቀድሞው ታጋይ ሴቶች እንደሚዘምሩት « እኔስ እወድቃለሁ በእምባሽ በኩረው ላይ ስትሸማቀቂ ሲከፋሽ እንዳላይ » ብለን የትግል ጥሪ ለእናቶቻችን፣ እህቶቻችን ብሎም ልጆቻችን በሞላ እናስተጋባለን።

የታሰሩት ይፈቱ !!!

የሰብ አዊ መብት ረገጣ ይቁም !!!

የሴቶች መብት እንዲከበር እንታገል !!!

www.aesed.org

aesed.iewo@gmail.com